Washington State Office of the Attorney General

# ኃይል አጠቃቀምን ሪፖርት ማድረግ፣ መመርመር እና መገምገም

## ምርጥ ተሞክሮዎች

ጁላይ 1፣ 2022

# ምርጥ ተሞክሮዎች ኃይል አጠቃቀምን ሪፖርት ለማድረግ፣ ለመመርመር እና ለመገምገም

**<u>ዋና መርህ</u>፡- ለሕዝብ ተጠያቂ ለመሆን እና የኤጀንሲን የፖሊሲ ልማት እንዲሁም የሥልጠና ፍላጎቶችን ለመገምገም፣ እያንዳንዱ የአካላዊ ኃይል እና ገዳይ ኃይል አጠቃቀም እንዲሁም የጦር መሣሪያ ወደ ሰው የማነጣጠር ሁኔታዎች በውስጥ ሪፖርት መደረግ እና በእዝ ሠራተኞች ትርጉም ያለው ግምገማ ሊደረግባቸው ይገባል።**

**ኤጀንሲዎችም አንዳንድ የኃይል አጠቃቀሞችን ለስቴት የኃይል አጠቃቀም መረጃ ፕሮግራም የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው (ለሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች Revised Code of Washington (RCW፣ የተሻሻለው የዋሺንግተን ደንብ) 10.118.030 ን ይመልከቱ)።**

# የኃይል አጠቃቀምን ሪፖርት ማድረግ

(1) ኦፊሰሮች ማንኛውንም አካላዊ ወይም ገዳይ ኃይል ከተጠቀሙ በኋላ ወዲያውኑ ለተቆጣጣሪዎቻቸው ማሳወቅ አለባቸው። ይህ ግዴታ ኃይል የተጠቀመውን ኦፊሰር ይመለከታል። የኃይል እርምጃ ሲወሰድ የተመለከቱ ኦፊሰሮችም ኃይሉ ለተቆጣጣሪ ሪፖርት መደረጉን ማረጋገጥ አለባቸው። የኃይል አጠቃቀምን ተከትሎ ለአንድ ተቆጣጣሪ የማሳወቅ ግዴታ የኃይል እርምጃ በተወሰደበት ሰው ወይም በሌሎች የቀረበን ማንኛውንም ቅሬታ ወይም ውንጀላ ያካትታል።

(2) ኤጀንሲዎች ገዳይ የሆኑ የኃይል እርምጃ ክስተቶችን የሚመለከቱ ሪፖርት አጻጻፍ ፕሮቶኮሎች ሊኖራቸው ከሚችሉበት ከገዳይ ኃይል አጠቃቀም በስተቀር፣ አካላዊ ኃይል የሚጠቀሙ ወይም አካላዊ የኃይል እርምጃ ሲወሰድ በቦታው የሚገኙ ኦፊሰሮች፣ እንደ የኦፊሰር መጎዳት ያሉ ከልካይ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር፣ ፈረቃው ከማለቁ በፊት የኃይል እርምጃ መወሰዱን ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው። ማንኛውም የኃይል እርምጃ አጠቃቀም ሪፖርትን የሚያዘገዩ ሁኔታዎች መመዝገብ አለባቸው።

   (a) ሽጉጡን ሰው ላይ ማነጣጠር ሪፖርት ሊደረግ የሚችል የኃይል እርምጃ አጠቃቀም ነው።

   (b) ህግ አክባሪን የእጅ ማሰር ሪፖርት አይደረግም፤ ነገር ግን ኦፊሰሮች የእጅ ካቴና ማድረግ ህመም፣ እንዲሁም መቧጨርን፣ ቁስልን፣ ሰንበሮችን ሲያስከትል ወይም ሌሎች በእጅ ካቴና ወይም የእጅ ካቴና በማሰር የሚያደርሱ ጉዳቶች መመዝገብ አለባቸው።

(3) የሪፖርት ይዘት

ኦፊሰሮች አካላዊ ወይም ገዳይ ኃይልን ለመጠቀም እና የተለየ የኃይል መሳሪያ ወይም ዘዴ ለመጠቀም የወሰዱትን ውሳኔ ለማስረዳት የተወሰኑ እውነታዎችን ማቅረብ አለባቸው። ሪፖርቶች የክስተቱን ዝርዝሮች በማብራራት እና ለተስተዋሉ ባህሪያት እንደ "የጦር እርምጃ ወሰደ" ወይም "የመዋጋት አቋም ያዙ" ያሚሉ ጠቅለል ያሉ ወይም ግልጽ ያልሆኑ ሀረጎችን በማስወገድ ገላጭ መሆን አለባቸው።

የኃይል እርምጃ አጠቃቀም ሪፖርቶች የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለባቸው፡-

   (a) በኦፊሰር እና የኃይል እርምጃ በተሰወሰደበት ሰው መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ግንኙነት የተደረገበትን ምክንያት፣ ለኃይል አጠቃቀም ያደረሱ እና በኃይል እርምጃ አጠቃቀም ጊዜ የነበሩ የዚያ ሰው እና የኦፊሰሩ ተግባሮች እንዲሁም የተጠቀሙበት ኃይል ልዩ ዓይነት እና መጠን የሚያብራራ የክስተቱ ማጠቃለያ፤

   (b) ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም የተሞከሩ የማረጋጋት ጥረቶች ወይም እንዳቸውንም ያልተጠቀሙበት ወይም ያልሞከሩበት ምክንያቶች፤

   (c) በኦፊሰሩ ላይ ወይም በሌላ ሰው ላይ የነበረ ማንኛውንም የአደጋ ሥጋት ወይም አካላዊ የኃይል እርምጃ የተወሰደበት ሰው የታጠቀ መሆኑን ለማመን መሰረት የሆነውን ነገር ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን ለእያንዳንዱ የኃይል እርምጃ አጠቃቀም እና ዓይነት ምክንያት የሆኑ ነገሮች፤

   (d) ሌሎች የኃይል እርምጃ የሆኑ ወይም የኃይል እርምጃ ያልሆኑ የታክቲክ አማራጮች የነበሩ እንደሆነ፤

   (e) ኦፊሰሮች እራሳቸውን የገለጹበት መንገድ፣

   (f) የኃይል እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የተሰጠ ማንኛውም ማስጠንቀቂያ እና እሱን ለማክበር የተሰጠ ጊዜ፣ ወይም ያልተሰጠበት ምክንያቱ፤

   (g) የተሳትፉ አካላት እና ምስክር የነበሩ ኦፊሰሮች፤

(h) የሲቪሎች ምስክሮች ስም እና አድራሻ መረጃ፤
(i) በክስተቱ ጊዜ የነበረ የኦፊሰሩ ሁኔታ (ማለትም፣ ዩኒፎርም ወይም የሲቪል ልብስ፣ ምልክት የተደረገበት ወይም ምልክት የሌለው ተሽከርካሪ፣ ብቻውን ወይም ከሌሎች ኦፊሰሮች ጋር መሆኑ እና አለመሆኑ)፤
(j) የሚታወቅ ከሆነ፣ ስም፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ዘር እና ጎሳን ጨምሮ የኃይል እርምጃ የተወሰደበት ሰው መረጃ፤
(k) ከኦፊሰሩ ጋር ሲነጻጸር የኃይል እርምጃ የተወሰደበት ሰው መጠን እና የሰውነት አቋም፤
(l) የኃይል እርምጃ የተወሰደበት ሰው የባህሪ ጤና ቀውስ እንዳለው የሚያሳይ ማንኛውም ማስረጃ፤
(m) እርጉዝ፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ ጎልማሳ የሚመስሉ እንደሆነ፤ የአካል ጉዳት ወይም የአካል እክል ምልክቶች የሚያሳዩ እንደሆነ፤ ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ የነበራቸው እንደሆነ፤ ወይም በልጆች ፊት የነበሩ እንደሆነ ጨምሮ የኃይል እርጃ የሚወሰድበት ሰው ሌሎች ባህሪያት እና ሁኔታን የተመለከተ መረጃ፤
(n) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማሰርን፣ ቁጥጥር ስር ማዋልን ወይም የህግ ማስከበሪያ እርምጃን የሚደግፉ እውነታዎች፤
(o) ድጋፍ ሰጭ ወይም ሌላ ግብዓቶች ተጠይቀው እንደሆነ እና ከሆነ፣ የደረሱበት ጊዜ፤
(p) በኦፊሰሩ፣ የአካላዊ ኃይል እርምጃ በተወሰደበት ሰው ወይም በምስክሮች ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም ቅሬታ መግለጫ፤
(q) በኦፊሰሩ የሚታወቅ ከሆነ በቦታው ላይ የተሰጡ የመጀመሪያ እርዳታ እና የሕክምና እርዳታዎች፤ እንዲሁም
(r) ለተቆጣጣሪ የተሰጠ ማሳወቂያ እና ተቆጣጣሪ ለክስተቱ ምላሽ የሰጠ ወይም ከክስተቱ በፊት ወይም በወቅቱ አማክረውት እንደሆነ።

(4) electronic control weapon (ECW፣ የኤሌክትሮኒክስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ) የሚተኩሱ ኦፊሰሮች የሚከተሉትን ሰነዶችም እንዲሁ ማቅረብ አለባቸው፡-
(a) የ ECW ስሪት፣ ሞዴል፣ ሰሪያል ቁጥር፤
(b) የ ECW ማስነሻ ቁጥር እና አጠቃላይ የመተኮሻ ጊዜ፤
(c) ጥቅም ላይ የዋለው የሞዴል አይነት (በተለዩ ሁኔታዎች መሰረት ፕሮብ ወይም ድራይቭ ስታን)፤
(d) ፕሮቡ/ECW ሰውየውን ያነካበት ቦታ እና የልብስ አይነት፣ ካለ፣ ያጋጠማቸው ፕሮቦች፣ እና፤
(e) የጦር መሣሪያን ውጤታማነት ለመገምገም አግባብነት ያለው መረጃ (ማለትም፣ ፕሮቦች ሰውየውን የነኩ እንደሆነ፣ ካልሆነ፣ ለምን እንዳልሆነ - ለምሳሌ፣ የሰውየው ወፍራም ልብስ፣ ሰውየው በጣም ሩቅ ነበር፣ ወዘተ)።

(5) ምስክር ኦፊሰሮች ምልከታዎቻቸውን እና ድርጊቶቻቸውን የሚገልጽ ገለጻ ማቅረብ አለባቸው።
(6) የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች በስቴት አቀፍ የኃይል መረጃ አሰባሰብ ፕሮግራም የሚፈለጉትን አካላዊ እና ገዳይ የኃይል ክስተቶች መረጃ መስጠት አለባቸው። (RCW 10.118.030).

## የኃይል አጠቃቀምን መመርመር እና መገምገም

(1) ለሞት፣ለከባድ የአካል ጉዳት ወይም ለአካል ጉዳት፣ የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች በዳይሬክተሩ በተቋቋመው አሰራር መሰረት Office of Independent Investigations (የገለልተኛ ምርመራ ቢሮን) ወዲያውኑ ማግኘት አለባቸው (RCW 43.102.120)።

(2) በአንድ ኦፊሰር የኃይል አጠቃቀም ምክንያት ለሚከሰት ጉዳት ወይም ቅሬታ (ለጊዜያዊ ምቾት ማጣት አይደለም)፣ ሆስፒታል መተኛት ወይም የሰው ሞት፣ ተቆጣጣሪዎች ወዲያውኑ ለሚመለከተው የእዝ ሰራተኛ ያሳውቃሉ።

(3) አካላዊ ኃይልን የተጠቀመ ወይም ያየ፣ የመራ ወይም አካላዊ ኃይል ጥቅም ላይ እንዲውል ያዘዘው ተቆጣጣሪ፣ ለክስተቱ የመርማሪም ሆነ የገምግሚ ተቆጣጣሪ ተግባር እና ኃላፊነት መወጣት የለበትም። ይህ ሁኔታ በሚከሰትበት ጊዜ፣ የመርማሪውን ወይም የገምጋሚውን ተቆጣጣሪ ተግባራት እና ኃላፊነቶችን ለማከናወን ያልተሳተፈ ተቆጣጣሪ መመደብ አለበት።

(4) <u>የተቆጣጣሪ ኃላፊነቶች፡- ምርመራ</u>

አካላዊ የኃይል እርምጃ እንደተወሰደ እንዲያውቅ ሲደረግ፣ ተቆጣጣሪው የተወሰደው ዝቅተኛ ደረጃ አካላዊ ኃይል መሆኑ ካልተነገረው በስተቀር፣ ተቆጣጣሪው በተገቢ ጊዜ የሚገኝ ከሆነ ለክስተቱ ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት አለበት፣

እንዲሁም ተገቢውን ምርመራ ማካሄድ አለበት። ምንም እንኳን ዝቅተኛ አካላዊ ኃይል በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል መመዝገብ እና መገምገም ቢኖርበትም፣ ዝቅተኛ አካላዊ ኃይል ብቻ በክስተቱ ከተወሰደ፣ ተቆጣጣሪዎች ምርመራ ለማካሄድ በቦታው ላይ ምላሽ መስጠት አያስፈልጋቸውም።

ከዝቅተኛ ደረጃ አካላዊ ኃይል የሚበልጥ አካላዊ ኃይል እርምጃ ሲወሰድ፣ ተቆጣጣሪው ለቦታው አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ካልተገኘ ምክንያቱን ይመዘግባል።

ገዳይ ኃይልን ላላስተናገዱ ክስተቶች፣ ተቆጣጣሪው የሚከተሉት ደረጃዎች ማጠናቀቃቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፦

(a) የክስተቱን ቦታ መጠበቅ እና መቆጣጠር።

(b) ሁሉም የተጎዱ ወገኖች በጊዜ የሕክምና እርዳታ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ።

(c) በክስተቱ ውስጥ የተሳተፉትን፣ ክስተቱን የተመለከቱ ወይም በተከሰተበት ጊዜ በቦታው ላይ የነበሩትን ሁሉንም ኦፊሰሮች መለየት። እንደ ኦፊሰር ጉዳት ያለ ከባድ ሁኔታ ይህንን ካልከለከለው በስተቀር፣ በተፈቀደው መሰረት የክስተቱን አጠቃላይ ሁኔታ ከተሳታፊዎች እና ምስክር ኦፊሰሮች ጋር መወያየት እና ሪፖርቶቻቸውን በስራ ፈረቃቸው መጨረሻ ላይ መጠናቀቁን ማረጋገጥ።

(d) አካላዊ ኃይል እርምጃ የተወሰደበትን ግለሰብ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ እና ከተቻለ ሚራንዳ መብታቸውን በማክበር ቃለ መጠይቁን ለመመዝገብ መሞከር።

(e) የሲቪል ምስክሮችን መለየት። ተቆጣጣሪዎች በቦታው ለመቆየት ፈቃደኛ ያልሆነውን ምስክር ማቆየት ወይም ማዘግየት የለባቸውም፤ ሆኖም የምስክሮቹ አካላዊ መግለጫ፣ የእውቂያ መረጃ፣ ሌሎች መለያዎች (ለምሳሌ የመንጃ ፈቃድ)፣ የሚታወቅ ከሆነ እና ማንኛውም የምሥክርነት መግለጫዎች መመዝገብ አለባቸው።

(f) ጉዳቶችን እና የተሰጡ ውይም ውድቅ የተደረጉ የመጀመሪያ እርዳታዎችን መመዝገብ።

(g) የኃይልን እርምጃ ሰለባውን እና ማንኛውንም ጉዳት የደረሰባቸው ኦፊሰሮች ጨምሮ ሁሉንም ጉዳቶች ወይም ተጎድቻለሁ የሚሉትን ፎቶ ማንሳት።

(h) ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ ብርሃንን፣ የአየር ሁኔታን፣ የተሽከርካሪ አቀማመጥን፣ የሽፋን ቦታን ወይም ሌላ ተዛማጅ መረጃዎችን እንዲያሳይ አድርጎ የክስተቱን ቦታ ፎቶ ማንሳት።

(i) ኦፊሰሮች በሰውነት ላይ የሚለበሱ ካሜራዎችን ከታጠቁ፣ የአካላዊ ኃይል አጠቃቀምን የሚያሳዩ ተዛማጅ ምስሎችን ውሰዱ እና ገምግሙ።

(j) ከአካላዊ ኃይል አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ሁሉም ማስረጃዎች ፎቶ መነሳታቸውን፣ መሰብሰባቸውን እና የተመዘገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

    i. በአካባቢው ያሉ ክትትል ካሜራ እና የግል ቤት ካሜራዎችን ጨምሮ ክስተቱን የቀረጸውን ማንኛውንም የሶስተኛ ወገን ቪዲዮ መለየት፣ ቦታዎችን መመዝገብ እና ቀረጻውን ለማምጣት መሞከር። ማየት ወይም ማውጣት ካልቻሉ ምክንያቱን መዝግቡ። ምንም ካልተገኘ፣ ምንም እንዳልተገኘ መዝግቡ።

    ii. ለ ECW አጠቃቀም፣ ካርትሬጆችን፣ ፕሮቦች፣ ሊዶች እና የ ECW ውሂብ ማውረጃ ቅጂዎች ሰብስቡ።

(k) ለግለሰቡ ወይም ለባለስልጣኑ የህክምና እርዳታ የገመገሙ ወይም የሰጡ የህክምና ባለሙያዎችን መለየት።

(l) ማንኛውም የስነምግባር ጉድለት ወይም ሊከሰት የሚችል የወንጀል ድርጊት ወዲያውኑ ለሚመለከተው የትእዛዝ ሰራተኛ ሪፖርት መደረግ አለበት።

(5) <u>የተቆጣጣሪ ኃላፊነቶች፦ መገምገም</u>

(a) ተቆጣጣሪው ሙሉነት፣ ትክክለኛነት እና ወቅታዊነት ለማረጋገጥ ሁሉንም ሰነዶች እና የክስተቱን ማስረጃዎች በወቅቱ መመርመር አለበት። ተቆጣጣሪዎች በግምገማቸው ወቅት የወሰዱትን እርምጃ መመዝገብ አለባቸው (ለምሳሌ፡ ሁሉንም የሚገኙትን ሪፖርቶች መገምገም፣ በኤጀንሲው የተቀዳ ቪዲዮ፣ የሶስተኛ ወገን ቪዲዮ፣ የምስክሮች መግለጫዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ሌሎች የምርመራ መረጃዎች ወይም ምልከታዎች)።

(b) ለተጨማሪ ዝርዝሮች ወይም ማብራሪያ ተቆጣጣሪው ያልተሟላ ወይም በቂ ያልሆነ የኃይል ሪፖርቶችን ይመልሳል።

(c) ተቆጣጣሪው የኃይል አጠቃቀሙ የኤጀንሲው ፖሊሲን ያከበረ እንደሆነ የመጀመሪያ የጽሁፍ አስተያየት ይሰጣል። በተጨማሪም ተቆጣጣሪዎች በክስተቱ የተነሱትን ማንኛውንም ፖሊሲ፣ ስልጠና፣ ታክቲካል፣ ቁጥጥር፣ እቅድ እና ማስተባበር፣ የኃይል አማራጮች ምርጫ፣ መሳሪያ እና ከአደጋ በኋላ የስነምግባር እና የአፈጻጸም ጉዳዮችን በመለየት እነዚህን ስጋቶች እና ምክሮችን መዝግቦ መያዝ አለባቸው።

(d) ተቆጣጣሪዎች የኃይል ግምገማ አጠቃቀማቸውን በፍጥነት ያጠናቅቃሉ እና ግምገማቸውን እና የሃይል ሪፖርቶችን እና ምርመራን ለዕዝ ሰንሰለቶች ግምገማ ያቀርባሉ።

(6) <u>የእዝ ግምገማ</u>

(a) በእዝ ሰንሰለት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ገምጋሚ የኃይል ሪፖርቶችን እና ምርመራን ትክክለኛነት፣ ማጠናቀቅ እና ወቅታዊነት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። እያንዳንዱ ገምጋሚ የአካላዊ ኃይል አጠቃቀም የኤጀንሲ ፖሊሲን የተከተለ ስለመሆኑ ሀሳባቸውን መዝግቦ እና ማንኛውም ፖሊሲ፣ ስልጠና፣ ታክቲክ፣ መሳሪያ ወይም አደጋ ከተከሰተ በኋላ የተነሱ ጉዳዮችን በመለየት ስጋቶቻቸውን እና ምክሮቻቸውን መመዝገብ አለባቸው።

(b) በመጨረሻም የኤጀንሲው ኃላፊ ወይም ተወካይ የአካላዊ ኃይል አጠቃቀም ከኤጀንሲው ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በመወሰን ማንኛውም ፖሊሲ፣ ስልጠና፣ ታክቲካል፣ ቁጥጥር፣ እቅድ እና ቅንጅት፣ የኃይል አማራጮች፣ መሳሪያዎች እና በድህረ-ክስተቱ የተነሱ የአደጋ ምግባር እና የአፈጻጸም ችግሮች መቀረፋቸውን ይለያል።

(c) አካላዊ ኃይል በተወሰደበት ሰው ወይም በሌሎች ግለሰቦች የቀረበ ማንኛውም የስነምግባር ጉድለት በኤጀንሲው የቅሬታ አሰራር መሰረት መመዝገቡ እና መመርመሩን ያረጋግጣል።

(d) በ RCW 43.101.135 በሚጠይቀው መሰረት ለ Criminal Justice Training Commission (ወንጀል ፍትህ ማሰልጠኛ ኮሚሽን) ሪፖርት ማድረግን ጨምሮ የኃይል ግምገማ የወንጀል ድርጊት ወይም የፖሊሲ ጥሰት መከሰቱን የሚያመለክት ከሆነ የትዕዛዝ ሰራተኞች ተገቢውን ማሳወቂያ እና ሪፈራል ማድረግ አለባቸው።

(7) <u>የሥልጠና ግምገማ</u>

የኤጀንሲው የሥልጠና አስተማሪዎች አዝማሚያዎችን ለመወሰን እና በአገልግሎት ውስጥ የሥልጠና እድገትን ለመምራት ሁሉንም የኃይል ሪፖርቶችን መገምገም አለባቸው።

(8) <u>የገዳይ ኃይል አስተዳደራዊ ምርመራ</u>

በምዕራፍ 43.102 RCW በተቋቋመው Office of Independent Investigations (የገለልተኛ የምርመራ ቢሮ) ወይም በ Washington Administrative Code (WAC፣ የዋሺንግተን አስተዳደራዊ ደንብ) 139-12፣ በተቋቋመው Independent Investigative Team (ገለልተኛ የምርመራ ቡድን) የሚመራ ገዳይ የኃይል ክስተቶችን ከኦፊሰሩ የወንጀል ምርመራ የተለየ እና ልዩ የወንጀል ምርመራን ተከትሎ፣ የሚመለከተው ኤጀንሲ ወቅታዊ የሆነ አስተዳደራዊ ምርመራ እና ገዳይ የኃይል ክስተቶችን በመገምገም የኤጀንሲው ፖሊሲና አሰራር መከበራቸውን ለማወቅ እና የስልጠና ፍላጎቶችን መለየት አለበት። አስተዳደራዊ ምርመራው ሲጠናቀቅ የሚመለከተው ኤጀንሲ Serious Incident Review Board መጥራት አለበት።

## የከባድ ክስተት ግምገማ ቦርድ

ሁሉንም የገዳይ ኃይል እርምጃን እና አንድ ሰው በእስር ላይ እያለ የሚሞትበትን ማንኛውንም ክስተት ጨምሮ፣ እያንዳንዱ የህግ አስከባሪ ኤጀንሲ ከባድ ክስተቶችን ለመገምገም Serious Incident Review Board (የከባድ ክስተት ግምገማ ቦርድን) ሊይዝ ይገባል። የግምገማው አላማ ክስተቱን በተጨባጭ ለመገምገም ነው ይህም (1) ኦፊሰሮች ሥልጣናቸውን በህጋዊ መንገድ እና ከኤጀንሲው የሚጠበቀው፣ ስልጠና እና ፖሊሲ ጋር በሚጣጣም መልኩ መጠቀማቸውን እና (2) ማንኛውንም አስፈላጊ የስልጠና ወይም የፖሊሲ ለውጦችን ለመለየት ነው።

ይህ የውስጥ ግምገማ ሂደት በ Office of Independent Investigations፣ በ Independent Investigative Team ወይም በሌላ የውጭ አካል ጉዳዩን ለመመርመር ወይም ለመገምገም ስልጣን ካለው ሌላ ምርመራ በተጨማሪ መሆን አለበት።

በኤጀንሲው አመራር ውሳኔ ማንኛውም የአካላዊ ኃይል አጠቃቀምን የሚመለከቱ ሁኔታዎችን ለመገምገም Serious Incident Review Board ሊጠራ ይችላል።

(1) **ጥንቅር**

የሚቻል ከሆነ ቦርዱ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

- (a) የኤጀንሲው መሪ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ያለው ተወካይ(ዎች)፤
- (b) በክስተቱ ውስጥ ያልተሳተፈ ሌላ የእዝ ሰራተኛ ወይም ተወካይ፤
- (c) የስልጠና ሰራተኞች፤ እና
- (d) ከአካባቢው ስልጣን ወሰን የመጣ የማህበረሰብ አባል ያልሆነ ኦፊሰር።

(2) **ወሰን እና ኃላፊነቶች**

ሁሉንም መግለጫዎች፣ ቃለመጠይቆች፣ ሪፖርቶች እና የክስተቱን ማስረጃዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ Serious Incident Review Board ሁሉንም የክስተቱን ገፅታዎች የመገምገም እና ከስልቶች፣ ከስልጠና፣ ከፖሊሲ እና ከመሳሪያዎች አንፃር ምክሮችን የማቅረብ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ቦርዱ ሊያገናዝባቸው የሚገቡ ቦታዎች በሚከተሉት ሲሆኑ ግን በዚህ አይወሰኑም፦

- (a) አካላዊ ኃይልን ከመጠቀም በፊት የሚቀድሙ ግንኙነቶችን እና እቅድን ጨምሮ ስልታዊ ውሳኔዎችን መስጠት፤
- (b) ኦፊሰሮች የማረጋጋት ስልቶችን የተጠቀሙበት መጠን፤
- (c) የማንኛውም የክስተቱ ቦታ ወይም የርቀት ክትትል ውጤታማነት፤
- (d) የሬዲዮ (ተላላኪን ጨምሮ) ግንኙነቶች ውጤታማነት፣
- (e) የተገቢ መሳሪያዎች ውጤታማነት እና መገኘት፤
- (f) የአሁኑ ፖሊሲ ለሚመለከታቸው ኦፊሰሮች በቂ መመሪያ የሰጠ እንደሆነ፤
- (g) ለቀረቡት ሁኔታዎች ኦፊሰሮችን ለማዘጋጀት የአሁኑ ስልጠና በቂነት፤
- (h) የክስተቱ ቦታ ላይ ኦፊሰሮች ወደ ማዳን ሁኔታ ምን ያህል ውጤታማ በሆነ መንገድ እንደተሸጋገሩ እና የመጀመሪያ እርዳታ እንዳቀረቡ ወይም እንዳመቻቹ ጨምሮ፣ ከክስተት በኋላ ውሳኔ መስጠት፤
- (i) ከጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች ጋር የተደረገ ግንኙነት (ለምሳሌ፣ Emergency Medical Technicians (EMT፣ የድንገተኛ ጊዜ የሕክምና ቴክኒሽያኖች)፣ ፓራሜዲክ)፤
- (j) ጉዳት ከደረሰባቸው ግለሰቦች ቤተሰብ ጋር ስለ ክስተቱ ለማሳወቅ የተደረገ ግንኙነት ውጤታማነት፤
- (k) የኃይል አጠቃቀምን ተከትሎ ማስረጃዎችን መያዝ እና ምስክሮችን መለየት ጨምሮ የተደረገ የቁጥጥር አፈፃፀም፤ እና
- (l) የክስተት ሪፖርቶች ጥራት።

(3) **የተግባር ነጥቦች**

- (a) Review Board ከቦርዱ ውይይቶች የሚነሱትን ሁሉንም ምክሮች እና የድርጊት መርሆች ለመመዝገብ፣ ለመተግበር እና ለመከታተል የሚያስችል መደበኛ ሂደት ሊኖረው ይገባል፣ ይህም ሲቻል ለህዝብ ግልጽነትን ይሰጣል።
- (b) በእያንዳንዱ የ Review Board ስብሰባ ማጠቃለያ ላይ ቦርዱ የሚመለከታቸውን ኦፊሰሮች፣ ምስክሮች ኦፊሰሮች እና ማንኛውም በቦታው ላይ ያሉ ተቆጣጣሪዎች በ Review Board የተለዩትን ጉዳዮች በተመለከተ አንድ አባል መሾም አለበት።
- (c) Review Board የተማሩትን ለሁሉም የኤጀንሲው ሰራተኞች ማስተላለፍ አለበት።

# የኃይል ክስተቶችን ገለልተኛ ኦዲት እና የኃይል የግምገማ ሂደት

ኤጀንሲዎች በውስጥም ሆነ በውጭ ስጋቶችን የሚፈጥሩ ከባድ የአካል እና የገዳይ ኃይል ክስተቶችን ለመገምገም ገለልተኛ ኦዲተርን ማሳተፍ አለባቸው። ኤጀንሲዎችም በየጊዜው ገለልተኛ ኦዲተር በማሳተፍ የኤጀንሲው የኃይል ፖሊሲዎች እና የኦፊሰሮቻቸውን የኃይል አጠቃቀምን በተመለከተ የሚጠበቁትን በስልጠና እና በኤጀንሲው የኃይል ግምገማ ሂደት ምን ያህል እየተተገበረ እንደሆነ መመርመር አለባቸው። የማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተሮች ግኝቶች እና ምክሮች በሕዝብ ሪፖርት ውስጥ መመዝገብ አለባቸው።

ኤጀንሲዎች ማንኛውንም ዓይነት ግምገማ ወይም ምርመራ ለሚያደርጉ ገለልተኛ ኦዲተሮች ሁሉንም ተዛማጅ ሰነዶችን ያለ ገደብ ማግኘት አለባቸው።